10 DECEMBER 2014 ተጻፈ በ የማ ናግሽ

# ‹‹ኤርፖርት ላይ እንደሚታነቁ የሚያምኑ ሰዎች ቢኖሩም ኢሕአዴግ ግን ስለመኖራቸውም አያውቅም››

በእንግሊዝ የኢትዮጵያ አምባሳደር ብርሃኑ ከበደ

አምባሳደር ብርሃኑ ከበደ እ.ኤ.አ. ከ **2007** ጀምሮ በእንግሊዝ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

አምባሳደር ብርሃኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የተቀላቀሉት ከ 35 ዓመታት በፊት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደተመረቁ ነበር፡፡ ለተወሰነ ጊዜ በብራስልስ ጀማሪ ዲፕሎማት ሆነው በመሥራት ላይ የነበሩት አምባሳደር ብርሃኑ ኢሕአዴግ ሥልጣን በያዘ ወቅት ወደ አገር ቤት ተመልሰው በተለያዩ ደረጃዎች ሠርተዋል፡፡ በተለይ የዓለም አቀፍ ዲፓርትመንት ጄኔራል ዳይሬክተር በነበሩበት ወቅት ወደ ተመድ ጠቅላላ ጉባዔ የሚጓዝ የመንግሥት ልዑካን ሁለተኛ ሰው በመሆን ለዘጠኝ ዓመታት ሠርተዋል፡፡ ከዚያም በሩሲያ ቀጥለውም በስዊድን አምባሳደር በመሆን አገልግለዋል፡፡  በቅርቡ በለንደን የአጭር ጊዜ ቆይታ ያደረገው የማነ ናግሽ ለንደን በሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተገኝቶ አምባሳደር ብርሃኑን ስለሁለቱ አገሮች ግንኙነት፣ የዳያስፖራ ፖለቲካና ተያያዥ ጉዳዮች አነጋግሯቸዋል፡፡

*ሪፖርተር፡- በአሁኑ ወቅት የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ግንኙነት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?*

አምባሳደር ብርሃኑ፡- የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ የመጣ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ውስጥ አንደኛ ደረጃ ይዛ ትገኛለች፡፡ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግንኙነቱ ዘርፈ ብዙ እየሆነ ነው የመጣው፡፡ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ዕርዳታ እንግሊዞች ‹‹Value for Money›› [ገንዘብን ለታሰበለት ዓላማ ማዋል] በሚል መርህ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጠው ዕርዳታ ለትክክለኛ ዓላማው እየዋለ መሆኑንና የሕዝብን ሕይወት በመለወጥ ተግባራዊ እየሆነ መሆኑን በደንብ አስቀምጠዋል፡፡ እንደ ምሳሌም ይጠቅሱታል፡፡ ለምሳሌ ባለፉት የሦስቱ ፓርቲዎች ጉባዔ የልማት ትብብር ፕሮግራም ውጤታማነት ሲገለጽ ኢትዮጵያ ለአብነት ነው የምትነሳው፡፡ ስለዚህ በጣም ውጤታማ የሆነ የልማት ትብብር አለ ብሎ መግለጽ ይቻላል፡፡

በንግድና በኢንቨስትመንት ዘርፍ ቀደም ሲል በጣም ትንሽ ነው የነበረው፡፡ በአሁኑ ወቅት ወደ 250 ሚሊዮን ፓውንድ ደርሷል፡፡ የኢትዮጵያ ምርቶች በብዛት ወደ እዚህ ወደ እንግሊዝ እየገቡ ነው፡፡ ብዙ መሠራት አለበት፡፡ የእኛ ምርቶች ለዚሁ ገበያ በሚመጥን መልኩ ጥራታቸው ከተሻሻለ ሰፊ የገበያ ዕድል አለ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የአበባ ምርት ይገባል፡፡ ቡና፣ ሻይ፣ የቆዳ ምርትና የጨርቃ ጨርቅ ምርቶች ይገባሉ፡፡

ትልቁ ነገር ግን በኢትዮጵያ ኢንቨስት የሚያደርጉ ኢንቨስተሮች ትልልቆች ናቸው፡፡ ለአብነት ለመጥቀስ ዲያጆ የሚባለው በኢትዮጵያ ውስጥ በ 225 ሚሊዮን ዶላር ሜታ ቢራ ፋብሪካን ገዝቷል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ 100 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስት አድርጓል፡፡ ስለዚህ በአጠቃላይ 325 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት አለው ማለት ነው፡፡ ዩኒሊቨር የሚባለው ትልቁ የመልቲላተራል ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመርያ የኢንቨስትመንት ኦፕሬሽን እየጀመረ ነው ያለው፡፡ ሦስተኛ ፒተርድ የሚባለው የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ድርጅት ለሰባ ዓመታት ጥሬ ቆዳ ይገዛ የነበረው በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሦስት ፋብሪካዎች ሠርቶ ከ 1,500 እስከ 2,000 ሠራተኞች ቀጥሮ እያሠራ ይገኛል፡፡ ይኼም የታወቀ ብራንድ ስለሆነ የቆዳ ውጤቶቹ ብሪቲሽ ኤርዌይስ የሚጠቀምበት ትልልቅ ሱቆች ውስጥ እየገባ ነው፡፡ ሌላ በማዕድን ፍለጋ ስንሄድ ታሎ በነዳጅ ፍለጋ ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ካምፓኒ ነው፡፡

አዮታ የሚባለው ደግሞ የወርቅ አምራች ድርጅት ገብቷል፡፡ ሌላ ዴሉክስ የሚባል የነዳጅ ፍለጋ ላይ የተሰማራ አለ፡፡ በዛ ያሉ ሌሎች ካምፓኒዎች ደግሞ በወርቅ ፍለጋ ላይ የተሰማሩ አሉ፡፡ ስለዚህ የኢንቨስትመንት አድማሱ እየሰፋ ነው፡፡

ሦስተኛ የፖለቲካ ትብብር ነው፡፡ በተለይ ዓለም አቀፍ ሽብርተኝነትን ከመቋቋም አኳያ ኢትዮጵያ አንድ ትልቅ አጋር ተደርጋ ነው የምትታየው፡፡ ኢትዮጵያ የተረጋጋና የቆየ የመንግሥት ሥርዓት ታሪክ ያላት እንደሆነች፣ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም ታማኝነት ያለው፣ ግልጽ ፕሮግራምና ስትራቴጂ ያለው መንግሥት እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡ ሌላው በአካባቢው ሰላምና ደኅንነት ዙሪያ ነው፡፡ አካባቢያችን እንደሚታወቀው ትንሽ ችግር የበዛበት ነው፡፡ በተለይ በሶማሊያና በደቡብ ሱዳን ያለው ሁኔታ ለመለወጥ በሚደረግ ጥረት የኢትዮጵያን ሚና በደንብ ያውቃሉ፡፡

የኤርትራ መንግሥት የሚያደርገው ፀረ ሰላም እንቅስቃሴ በደንብ የሚታወቅ ነው፡፡ በፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ መንግሥት ላይ ጫና እንዲደረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የኤርትራ መንግሥት ባህርያት በይበልጥ የሚረዳ መንግሥት እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ ተመድ የኤርትራ መንግሥት ይህንን ባህሪውን ለውጦ ወደ ሰላም እስካልመጣ ድረስ ጫናው መነሳት አለበት ብሎ የሚያምን ድርጅት ነው፡፡

*ሪፖርተር፡- ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ መንግሥት በቁጥጥር ሥር የዋሉት የእንግሊዝ ዜግነት ያላቸውን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጉዳይ በተመለከተ የእንግሊዝ መንግሥት ስሜት ምንድን ነው? ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን (በግላቸው) ለኢትዮጵያ መንግሥት የመማፀኛ ደብዳቤ መጻፋቸው ይነገራል፡፡*

አምባሳደር ብርሃኑ፡- ጉዳዩ ይህን ያህል ትልቅ ጫና የለውም፡፡ ነገር ግን ግለሰቡ የእንግሊዝ ዜጋ እንደመሆኑ መጠን በእንግሊዝ መንግሥት የሆኑ ዕርምጃዎች መወሰድ አለባቸው የሚሉ አሉ፡፡  ሰውየው ለምን ታሰረ የሚል አይደለም፡፡ በሕግ ይዳኝ የሚል ነገር ነው፡፡

አንደኛው ለእንግሊዝ ዲፕሎማሲያዊ ጉብኝት ተደራሽ ይሁን የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ከዚህ በፊት የተላለፈው የሞት ቅጣት ተግባራዊ እንዳይሆን የሚል ነው፡፡ ሦስተኛ ከየመን ወደ ኢትዮጵያ የተወሰደበትን ሁኔታ ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ ላይ ግልጽ የሆነ መልስ ነው ያለው፡፡ ለኤምባሲዎች የመጎብኘት ዕድል አንድ ጊዜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሒደትም ውይይት እየተደረገበት ነው፡፡ የሞት ቅጣት በሚመለከት በሕገ መንግሥቱ መሠረት የሚሄድ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ የሚሰጡት ፕሬዚዳንቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ በዚህ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ የሚሰጡበት አይሆንም፡፡ በየመንና በኢትዮጵያ የፀረ ሽብር ትግል ነው ተፈጻሚ የሆነው፡፡

አሁንም መጠየቃቸው አይቀርም፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ሕጋዊ ምላሽ እየሰጠበት ነው ያለው፡፡ ይኼ ሰውዬ የሽብር ተግባር ላይ ገብቷል፡፡ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ከሚፈልጉ ኃይሎች ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ይሠራ ነበር፡፡ ሦስተኛ ራሱም ይህንን አምኗል፡፡ ብዙ ጊዜ እጅ ከፍንጅ የተያዙና የታሰሩ ሰዎች እሱ እንደሚያሠለጥናቸውና የቡድኑ መሪ እንደሆነ፣ ከኤርትራ መንግሥት ጋር አብሮ እንደሚሠራ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር አለ፡፡ እሱ እንደተያዘ ግንቦት ሰባት የሚባለው ድርጅት ራሱ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጦርነት ነው ያወጀው፡፡

ስለዚህ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይኼ ሰውየ ወንጀለኛ አይደለም ብለው የሚገምቱ አይመስለኝም፡፡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እዩና የሞት ቅጣቱን ተግባራዊ አታድርጉበት የሚል ነው፡፡ ይኼ በሒደት በመግባባት የሚፈታ ነው የሚመስለኝ፡፡ እነሱ ዋና ትኩረት የሚሰጡት በእንደዚህ ዓይነት ነገሮች የሁለቱ አገሮች ግንኙነት እንዳይበከል ነው፡፡ ያው ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ድርጅቶች አሉ፡፡ እነ ሂውማን ራይትስ ዎች እና እነ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል አሉ፡፡ እነሱ በመንግሥት ላይ የሚቀሰቅሱት ውንጀላ ይቀጥላል፡፡ ውንጀላቸው መሠረት የለውም፡፡ ዲሞክራሲ በአንድ ሌሊት የምትፈጥረው አይደለም፡፡ የእንግሊዝ ወይም የኖርዌይ ዓይነት ካልሆነ ብለህ ዲሞክራሲ አይደለም ብለህ ልትፈርጅ አትችልም፡፡

ኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሒደቱን ትናንት የጀመረች አገር ነች፡፡ ምንም ዓይነት ስህተት አልተሠራም አይባልም፡፡ ስህተት የሒደቱ አካል ነው፡፡ ያንን ነው ለማስረዳት የምንሞክረው፡፡

በተለያዩ መድረኮች እንጋበዛለን፡፡ እናስረዳለን፡፡ መካድ አይደለም፤ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት ችግር የለም አይልም፣ እኔም እንደሱ አልልም፡፡ እንደዚያ በል ብሎኝም አያውቅም፡፡ እያስመዘገብነው ያለውን ውጤት ማስረዳት ነው፡፡

እንግዲህ በኤምባሲ ደረጃ በመንግሥት ደረጃም ማስረዳት አለብን፡፡ ከተራው ዜጋ ጀምሮ የኢትዮጵያን ሰላም ለሚፈልጉ በሙሉ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

ሪፖርተር፡- ቀደም ሲል የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ ሲፀድቅ የእንግሊዝ መንግሥት ከተቃወሙት መካከል ነበር፡፡ በእርግጥ ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሕጉ እንዳለ ቃል በቃል የተተረጎመው ከእንግሊዝ እንደሆነም ተናግረው ነበር፡፡ አሁንስ የእንግሊዝ መንግሥት በአዋጁ ላይ ያለው አቋም ምንድነው? የፖለቲካ መድረኩ ጠቧል የሚል አቋምም ነበረው፡፡
አምባሳደር ብርሃኑ፡- አዋጁ ላይ ሳይሆን ከመጀመሪያውም ያላቸው ቅሬታ አፈጻጸሙ ላይ ነው፡፡ መፍትሔው ጠንክሮ ማስረዳት ነው፡፡ በእርግጥ የፀረ ሽብርተኝነትና የሲቪል ማኅበራት አዋጆችን በድጋሚ እዩዋቸው የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ የተለያዩ ጉዳዮችን የምንወያይበት የጋራ መድረክ አለን፡፡ ግልጽ የሆነ ውይይት የምናደርግበት ነው፡፡

የፖለቲካ መድረኩ ጠቧል የሚል ቅሬታ አላቸው፡፡ አሁን ግን ራሳቸው የሚመሰክሩት ነው፡፡ የተቃውሞ መድረኩ ራሱ አገርን ረዥም ርቀት ለማስጓዝ የሚያስችል ቁመና ያለው አይደለም፡፡ ፕሮግራም ለሌለው አካል መድረኩ ኖረ አልኖረ ትርጉም የለውም፡፡ ይኼ ብዙዎቹ ፊት ለፊት የሚናገሩት ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ኢሕአዴግ ታሪክ የጣለበት ኃላፊነት አለ፡፡ መንግሥት ሆኖ አገር እየመራ ስለሆነ ኃላፊነት የሚሰጠው ተቃዋሚ አካል እንዲኖር ሚና አለው የሚል የወዳጅነት ምክር ይሰጣሉ፡፡ እኛም ያለውን ሁኔታ እናስረዳቸዋለን፡፡ አንዳንድ ችግሮች ግን አይጠፉም፡፡

ሪፖርተር፡- እንግሊዝ ውስጥ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ነው ያሉት፡፡ ከዳያስፖራው ጋር ያላችሁ ግንኙነት በምን ላይ የተመሠረተ ነው?
አምባሳደር ብርሃኑ፡- ጥሩ ነገር እየተሠራ ነው፡፡ አንደኛ ዳያስፖራው ስለአገሩ ብቁና ወቅታዊ መረጃ የሚያገኝበት ሥራ እየሠራን ነው፡፡ በኢንተርኔት ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ ከአቅም ግንባታ ጋር በተያያዙ በራሳችንና በተለያዩ ድረ ገጾች ቪዲዮ እንለቃለን፡፡ እዚህ ላለው ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ኢትዮጵያን ለማስተዋወቅ ጥሩ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ ሦስተኛ ሰዎች በተደራጀበት አካባቢ ቀርቦ የማነጋገር ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ ለምሳሌ የልማት ማኅበሮች አሉ፡፡ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች አሉ፡፡ ከእነሱ ጋር አብሮ ለመሥራት የተደረጉ ጥረቶች አሉ፡፡ ፕሮፌሽናል ባለሙያዎችንም በራሳቸው ተደራጅተው አገራቸውን እንዲረዱ እንሠራለን፡፡ የሐኪሞችና የኢንጂነሪንግና የአማካሪዎች ማኅበራትም አሉ፡፡ ከሐኪሞች ጋር ብዙ መሥራት ያለብን ይመስለኛል፡፡ አንዳንድ በጥባጭ የሆኑ ሰዎች አሉ፡፡ በአጠቃላይ ግን ትልቅ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ አይደሉም፡፡ የሚያሳድሩት ጫና የለም፡፡ ዋናው ነገር እኛ እዚህ ስለሆን አይደለም፡፡ የአገራችን ሁኔታ መለወጥ ነው፡፡ በውጭ ያለው ሕዝብ አገር ቤት ሂዶ የአገራችንን ሁኔታ በራሱ ያምናል፣ ሌሎችንም ያሳምናል፡፡ የእኛ ሥራ ያለውን ለውጥ ለማስረዳት መሞከር ነው፡፡ በዋናነት ግን ኤምባሲ ስለሠራ አይደለም፡፡ አገር ቤት ያለው ለውጥ ነው ሰው ሐሳቡን እንዲለውጥ የሚያደርገው፡፡ ሌላው ለዓለም ገበያ ለሽያጭ የቀረበውን ቦንድ በተመለከተ በውጭ የተሸጠ በጣም ጠቃሚ እንኳን ባይባል፣ የአውሮፓ አጠቃላይ ተደምሮ የዚህ የእንግሊዝ ይበልጣል፡፡ ወደ 1.4 ሚሊዮን ዶላር ቦንድ ሸጠናል፡፡
ሪፖርተር፡- አንዳንድ ሰዎች እንዳነጋገርኳቸው ኢትዮጵያ ውስጥ በተግባር ካለው የተለየ መረጃ ነው ያላቸው፡፡ እነዚህ ሰዎችን ደርሳችሁ ያለውን እውነታ ለማስረዳት ያደረጋችሁት ጥረት ምንድን ነው?

አምባሳደር ብርሃኑ፡- አንዳንዶ ራሱን ለመለወጥ የማይፈልግ አለ፡፡ ራሱ ያልሆነ ነገር ለማሳመን የሚፈልግ ሰው አለ፡፡ አንዳንድ ሰው በራሱ ቆይታ እዚህ አንዳንድ ምክንያት ይኖረዋል፡፡ መብቱ ነው፡፡ ነገር ግን እዚህ መቆየታቸው አገርን ጨለማ አድርገው እንዲያዩ ያደረጋቸው ሰዎች አሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ብትነግራቸውም ሊያዳምጡህ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም እዚህ በመቆየታቸው የሚያማቸው ነገር አለ፡፡ ስለዚህ ለህሊናቸው ሲሉ አገር ቤት ያለው ጨለማ ብለው ራሳቸውን የማሳመን ነገር አለ፡፡ ይህንን ምንም ማድረግ አትችልም፡፡ ሌላው በጥላቻ ላይ የተነሳ ፖለቲካ አለ፡፡ አንደኛ ጎጂ ነው፡፡ ሁለተኛ አገርን ወዴትም አቅጣጫ ሊወስድ የማይችል መጥፎ ፖለቲካ ነው፡፡ ይህንን መዋጋት ያስፈልጋል፡፡ መፍትሔው በምክንያትና መረጃ ማሸነፍ መቻል ነው፡፡ ወደሌሎች እንዳይተላለፍ ማድረግ ነው፡፡ እኛ ሁሉም የመንግሥት ደጋፊ እንዲሆን ምንም ፍላጎት የለንም፡፡ መንግሥትን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ መርህ ላይ መሠረተ አድርጎ ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ የሚቃወምና የሚተች በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በግልጽ ተቀብለን የማነጋገርና የማወያየት አካሄድ አለን፡፡ ብዙዎችን ቀርበህ ስትናገራቸው ጠንከር ያሉ ተቃውሞ የነበራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የገቡ አሉ፡፡

ሪፖርተር፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ እነዚህ ሰዎች ምን ይላሉ?

አምባሳደር ብርሃኑ፡- አንደኛ ብዙ የማያውቁት ነገር እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ ሁለተኛ አገር ቤት ያለው አመራር ከላይ እስከታች ሥነ ሥርዓት ያለው እንደሆነ፣ እውነተኞች እንደሆኑ መገንዘባቸውን ያስረዳሉ፡፡ ሄደው ሲያነጋግሯቸው አዲስ ነገር ለመማርና ለማወቅ ያላቸውን ትዕግሥት ያደንቃሉ፡፡ ምክንያቱም ሰዎቹ የነበራቸው አቋም ጠቅላላ ጨለማ ስለነበር ነው፡፡ አመራሩ ከሕዝብ የራቀ ድርጅቱ ሰዎችን የሚጨፈጭፍ ነበር የሚመስላቸው፣ የተለየ ሆኖ ነው የሚያገኙት፡፡ ልንታሰር ይሆናል የሚል ፍርኃት ያላቸው አሉ፡፡ ኢሕአዴግ 90 ሚሊዮን ሕዝብ የሚመራ ድርጅት ነው፡፡ እገሌ ወጣ እገሌ ገባ ብሎ ለመቆጣጠር ጊዜም የለውም፡፡ አንድም የተሳሳተ አመለካከት ነው አልያም ለራስ የሚሰጡት ግምት ነው፡፡ ሰው ከገደሉ ወይም ሌላ ወንጀል ከፈጸሙ ኢሕአዴግም ማንም አያድናቸውም፡፡ ሕግ ነው የሚመለከታቸው፡፡ ኤርፖርት ላይ እንደሚታነቁ የሚያምኑ ሰዎች አሉ፡፡ ኢሕአዴግ ግን ስለመኖራቸውም አያውቅም፡፡

ሪፖርተር፡- እዚህ ካለው የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ በቀጣይነት ተስፋ የምትጥሉበት በየትኛው የዕድሜ ክልል ያለውን ነው?

አምባሳደር ብርሃኑ፡- እንግዲህ በደርግ ጊዜ የነበረው የአስተሳሰብ ልዩነት አለ፡፡ እሱ የእኔ ትውልድ ነው፡፡ አሁንም ድረስ ከጭንቅላታቸው ያልወጣ ሰዎች አሉ፡፡ ምናልባትም በልጆቻቸውም ላይ ተፅዕኖ በመጠኑ የሚያሳድሩ ይሆናል፡፡ ሆኖም ይኼ አስተሳሰብ እየተዳከመ ነው፡፡

በየትኛውም አገር ያለው ግን የወደፊቱ ትውልድ አለ፡፡ ኢንቨስት ማድረግ ያለብን በዚህ ትውልድ ላይ ነው፡፡ ምንም የተሸከመውና የተበላሸ አስተሳሰብ የለውም፡፡ ምክንያቱም በአገር ቤት አባት እናት የሚለው የለውም፡፡ አባት እናት እዚህ ነው ያሉት፡፡ ዘመዶቹ ወንድሙ እዚሁ ነው ያሉት፡፡ ይህንን ከሥሩ ለማገናኘት ከፍተኛ ሥራ ይጠብቀናል፡፡ በእርግጥ ከዚህ ጋር በተያያዘ በዳያስፖራ ፖሊሲ ውስጥ አንድ የተያዘ ፕሮግራም አለ፡፡ ኤምባሲው ውስጥ ወይም አገር ቤት ሄደው የሚሠሩት በኢንተርናሽናል ፕሮግራም የተወሰኑ ልጆች አሉን፡፡ እኛ ጋ ለተወሰኑ ወራት ሠርተው ይሄዳሉ፡፡ ያ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

ሪፖርተር፡- ቅድም ያነሱልኝ ከጥላቻና ከፖለቲካ አክራሪነት ጋር በተያያዘ አንድ ተቃራኒ ነገር አለ፡፡ ዳያስፖራ ውስጥ ያሉት አንዳንድ ሰዎች አገር ቤት ካለው የጥላቻና የዘረኝነት ፖለቲካ የባሰ ያንፀባርቃሉ ይባላል፡፡ እዚህ የዲሞክራሲና የሠለጠነ ፖለቲካ ውስጥ እየኖሩ የተሻለ የዲሞክራሲ ባህልን ማሳየት እንዴት ተሳናቸው?

አምባሳደር ብርሃኑ፡- ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሳይካታሪስት ባለሙያ መሆን ይጠይቃል፡፡ እኔ ራሴንም ሁሌ የምጠይቀው ነው፡፡ በእርግጥ ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ሰዎች ናቸው፣ ነገር ግን ድምፃቸው ከፍ ብሎ የሚሰሙ ናቸው፡፡ ያለውን ዘመናዊና ሶሻል ሚዲያ ለተበላሸ ዓላማ ሲያውሉ ታያለህ፡፡ ይኼ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለጥፋት እየተጠቀሙበት ነው፡፡ አብዛኛው ዳያስፖራ ይህንን አይቀበልም፡፡ ቢያንስ ለዘመዶቹ ሰላም ይጨነቃል፡፡ ይኼ የጥቂቶች አስተሳሰብ ብዙዎቹ ዳያስፖራዎች ይገልጻቸዋል ወደሚል ድምዳሜ እንዳናመራ መጠንቀቅ አለብን፡፡ እነዚህ ሰዎች ግን ማንነታቸውን ማጋለጥ አለብን፡፡ ኤምባሲዎች ይህንን መሥራት አለባቸው፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ አገር ቤት ያለው የኮሙዩኒኬሽን ክህሎታችን መሻሻል አለበት፡፡ ምክንያቱም ቀድመህ ያለህን ነገር መሸጥ ስትችል መናገር ሳትችል ነው ስለአንተ መታወቅ የሚችለው፡፡ እዚህ ላይ ሰፊ ክፍተት አለን፡፡ ሰፊ ኢንቨስትመንት ማድረግ አለብን፡፡ መሥራት የምንችለውን በራሳችን ካልሆነ ደግሞ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመሆን መሥራት ይኖርብናል፡፡ እኛ ብቻ ሳንሆን ያደጉት አገሮችም ይጠቀማሉ፡፡

ሪፖርተር፡- የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በውጭ ላሉት ኢትዮጵያዊያን እምብዛም ናቸው ይባላል፡፡

አምባሳደር ብርሃኑ፡- አንድ ኤምባሲ አቅሙ የፈቀደውን ያህል መሥራቱ አይቀርም፡፡ ግን አንዳንዱ ዕርዳታ የሚጠይቅበት መንግሥት ራስህን ክሰስና እኔን ዕርዳኝ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆንኩ ማረጋገጫ ስጠኝ የሚል አለ፡፡ ይኼ ከመንግሥት መርህ ጋር የሚጋጭ ነገር ነው፡፡ ከዚህ አገር ሕግ ጋር የሚጋጭ ነገር አንሠራም፡፡ መረዳት የለባቸውም ማለት አይደለም፡፡ ዜጎቻችንን ባገኘነው ዕድል ሁሉ መርዳት አለብን፡፡ ግን አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ማነቆዎች ውስጥ ትገባለህ፡፡ የመንግሥትን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ፣ ሕጎች የሚጣረሱበት፣ ያን ጊዜ አንድ ቀይ መስመር ማስቀመጥ አለብህ፡፡ በዓረብ አገር ያሉት ኤምባሲዎቻችን ግን 24 የሚሠሩበት ጊዜ አለ፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ጨምሮ፡፡ ያ ማለት ግን አገልግሎት አሰጣጣችን በሙሉ ማሻሻያ አያስፈልገውም ማለት አይደለም፡፡  ለመርዳት ግን ቀናነት አለ፡፡

ሪፖርተር፡- ከህዳሴ ግድቡ ጋር በተያያዘ የእንግሊዝ አቋም ምንድን ነው? እዚህ ላይ የሠራችሁት ሥራ አለ?

አምባሳደር ብርሃኑ፡- አዎ! የእንግሊዝ አቋም ችግራችሁን በድርድር ፍቱት የሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ታሪካዊ ሚና አላቸው፡፡ ዓባይ ላይ እ.ኤ.አ. የ 1929 ስምምነት በወቅቱ የራሳቸው ጥቅም ለማስጠበቅ በእነሱ የተፈረመ ነው፡፡ በእኛ በኩል ስለዓባይ የምናስረዳው ግንዛቤ አለ፡፡ ምን ያህል እንደምናመነጭ፣ ግድቡ የሌሎችን ጥቅም ለመጉዳት እንዳልሆነ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ቡድን ያመጣው ሪፖርት ለማስረዳት እንሞክራለን፡፡ አንዳንዶም በዚህ ላይ ዕውቀት ያላቸው ፕሮፌሰሮች ጠርተን ጉባዔ አዘጋጅተን ገለጻ እንዲደረግ አድርገናል፡፡ ገንዘብ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ስለጉዳዩ አጋሮቻችን በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

ሪፖርተር፡- ቀደም ሲል የእንግሊዝ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ጋር ባደረጉት ውይይት ከዕርዳታ ይልቅ ንግድን ለማስቀደም ተስማምተው ነበር፡፡ በእሱ መሠረት እየሠራችሁ ነው?

አምባሳደር ብርሃኑ፡- ትልቁ መርህ ዕርዳታ አሸጋጋሪ ድልድይ እንጂ በራሱ ውጤት አይደለም፡፡ ዋናው ነገር ንግድና ኢንቨስትመንት ነው፡፡ በንግድና ኢንቨስትመንት የሚደረገው ግንኙነት የጋራ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ የአገሮች ጥቅም ያስተሳስራል፡፡ ሰጪው አገር ዕርዳታ በረዥም ጊዜ የራሱ የሆነ ጥቅም አለው፡፡ አንደኛ ዓለም አቀፍ ግዴታቸውን የመወጣት ኃላፊነት ነው፡፡ ሁለተኛው ግን ዕርዳታ ላደረገለት አገር አርቆ የሚያያቸው ጥቅሞች ይኖራሉ፡፡

ከዕርዳታ ወደ ንግድና ኢንቨስትመንት መሄድ ተቀባይነት ያለው መርህ ነው፡፡ ያንን ለማድረግ የእንግሊዝ የተለያዩ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ ሄደው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማድረግ ነው፡፡ እዚህ በተሳካ ሁኔታ አድርገናል፡፡ ሁለተኛ እ.ኤ.አ. በ 2011 ትልቅ የኢንቨስትመንት ፎረም ነበር፡፡ በእርግጥ የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር

[ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እያሉ] መርተው በመጡት የመንግሥት ልዑክ ወደ 44 ለሚሆኑ ድርጅቶች ትልቅ ገለጻ አድርገውላቸዋል፡፡ የተሳካ ነበር፡፡ በውጤቱ ብዞዎቹ ኢትዮጵያ እየገቡ ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ያስመዘገበቻቸውን ውጤቶች እያስረዳን፣ ‹‹ኢትዮጵያ የመጭው ጊዜ ምርጫ ነች›› የሚለውን በደንብ ማስረጽ ያስፈልጋል፡፡ ይኼ ግን የአንድ ጊዜ ሥራ አይሆንም፡፡ ሰዎች በጭንቅላታቸው የቀረፁት የድህነትና የድርቅ ምሥል ለማጥፋት ቀጣይ ትግል ያስፈልጋል፡፡ ከ 30 ዓመት በፊት የነበረው ጉዳይ ታሪክ ነው፡፡ እሱ በቀጣይነት የሚሠራ ነው፡፡ እያስረዳን ነው፡፡ ውጤትም እየተገኘ ነው፡፡ አሁን ባለው አመለካከት አፍሪካ ውስጥ በማደግ ላይ ያለው ኢኮኖሚ ሚናው እየበለጠ ነው የሚል ስሜት አለ፡፡